# የክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ደንቦች

የክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) አሰራር በፕሮግራሞችና ትምህርት ክፍል ካሉበት የክፍል ደረጃ በላይ በትምህርት ሂደት በፈጣነ ሁኔታ ወይም ከተለመደው በተለየ ሁኔታ በወጣትነት እድሚያቸው የፈጠኑ እንደሆኑ የሚታዩ የተወሰኑ ተማሪዎችን ካሉበት የክፍል ደረጃ ከፍ ባለ ደረጃ እንዲመደቡ የማድረግ አሰራር ነው። በክፍል ውስጥ የማስተማር ፕሮግራም በተለያየ መልኩ ሊከናወን ይችላል፤ ለምሳሌ የሥርዓተትምህርቱን ማጨክ ማብዛት ወይም ቴሌስኮፒንግ ( አሁኑ ካለበት የትምህርት ዓመት ባሻገር ያለው ካሪከለም ትምህርት መጨመር) እና በራስ አቅም መጠን ትምህርት መከታተል። በአንዳንድ ሁኔታ የዚህ ዓይነቱ የትምህርት አሰጣጥ ለተወሰኑ ተማሪዎች የሚፈለገውን የአካዳሚ ብቃት ላይሰጥ ይችላል። ይህም ተማሪው ካላበት ክፍል በላይ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲመደብ ውሳኔ ሊደረግ ይችላል።

የክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ውሳኔዎች አመቺ ጊዜ የሚሆነው ክፍል ከመጀመሩ አስቀድሞ ባለው የስፕሪንግ ወቅት ወይም በተቻለ መጠን የትምህርት ዓመት በተጀመረበት የመጀመሪያ ግዚያት ሲሆን ውሳኔው መካሄድ ያለበት በምርምር ላይ በተመሰረተ ወቅታዊ ምርጥ አሰራር ላይ ተመስርቶ መሆን አለበት።[1] የተሞላ የተማሪው መግለጫ (ፕሮፋይል ) መዘጋጀት ይኖርበታል ትክክለኛውን ምደባ ለመወሰን። በርካታ የዝግጅነት ታሳቢ ሁኔታዎች በጥቅም ላይ መዋል አላባቸው የአካዳሚ ብቃትን ፣ ማህበራዊ እና የባህሪ(ኢሞሽን) እድገት እና የቋንቋ እድገት ጭምር። መለኪያው ከፍተኛ ውጤት የሚያሳይ በአካዳሚ እና (ለምሳሌ፣ የተማሪው ችሎታ፣ አጠቃላይ እውቀት እና ውጤት ) እና ከአካዳሚ ውጭ የሆኑ ታሳቢ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፣ የእድገት ታሳቢ ሁኔታዎች እንደ እድሜ፣ የሰውነት መጠን፣ አካላዊ እንቅስቃሴ (የሞተር ኮኦርድኔሽን) የመግባባት ሁለገብ ችሎታ፣ የስሜት እድገት፣ ባህሪ ከእድሜ እኩዮች እና አስተማሪዎች ጋር ግንኙነት፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚደረግ ተሳትፎ ፣ አስተሳሰብ እና ድጋፍ)። የልዩ ትምህርት ወይም የእንግሊዘኛ ቋንቋ(EL) አገልግሎቶች ምደባ ተማሪውን ለክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ከመታጨት አይገድበውም።

## I. <u>ትርጎሜዎች</u>

### A. **አንደኛ ክፍል ቀድሞ መጀመር**

በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በእድሜው መግባት የማይችል ቢሆንም እንኳ ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚመጥን ትምህርት ለመስጠት ተማሪውን ወደ አንደኛ ክፍል የማስገባት አሰራር።

### B. **ሙሉ ክፍል መዝለል (ክፍል መዝለል - አክስለሬሽን)**

ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚመጥን ትምህርት ለመስጠት ከእድሜው አንፃር ሊኖርበት ከሚገባው ክፍል በመዝለል(አክስለሬሽን) ተማሪ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ የክፍል ደረጃ ትምህርት ሙሉ ጊዜውን እንዲከታተል የማድረግ አሰራር።

---

[1] ከቴምፒልተን ሪፖርት(Templeton Report) (2004) የመነጨው ፤ የምርምርና እና ፖሊሲ ኢኒስቲትዩት(IRPA) *"A Nation Deceived: How Schools Hold Back America's Brightest Students,"* በሚል ርእስ ከተዘጋጀው እና የ10 ዓመታት ውጤት ንፅፅር "A Nation Empowered" (2015) ቀጣይነት ያለው ከክፍል መዝለል - (አክስለሬሽን) ጋር የተያያዘ አጠቃላይ ወቅታዊ የምርምር እና የተግባር አሰራር ይሰጣል። የዚህ ውጤት እንደሚጠቁመው በሌላ የተለየ የአቀራረብ(ዲፈረንሺሽን) ወይም የማበልፀጊያ (ኢንሪችመንት) አገልግሎቶች ፍላጎታቸው ላልተሞሉ ተማሪዎች ክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ከፍ ያለ የአገልግሎት አቀራረብ ሞዴል ነው። በተጨማሪም የቴምፒልተን ሪፖርት ማጠቃለያ ተማሪዎችን የአካዳሚ እና የማህበራዊ-የስሜት ፍላጎቶቻቸው በማደጉ ካሉበት የክፍል ደረጃ የበለጠ ከፍ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ሲሆን አንድ ሙሉ ክፍል እንዲዘሉ ማድረግ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ይገልፃል።

C. **በአንድ ትምህርት ዓይነት (በይዘት ላይ የተመሰረተ) ክፍል መዝለል**
ተማሪው ካለበት የክፍል ደረጃ ከፍ ያለ ክፍል ውስጥ ወይም ከፍ ያለ እድሜ ካላቸው ልጆች ጋር በአንድ ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ዓይነት ከትምህርት ቀኑ ከፊሉን ጊዜ እንዲከታተል ማድረግ ።

D. **ቀድሞ ምረቃ**
ለተማሪው ከፍ ያለ ትምህርት እድል በመስጠት ቢያንስ ከጊዜ ሰሌዳው አንድ ዓመት ማስቀደም። ይህ ሊከናወንበት የሚችለው መንገድ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመውሰድ በጥምር ፕሮግራም በመግባት ወይም በራስ ተነሳሽነት፣ የተፋጠነ ትምህርት በ ቲ. ሲ. ሳታላይት ግቢ በመከታተል ሊድረግ ይችላል።

E. **በአንድ ተመሳሳይ ጊዜ /ጥምር ምዝገባ**
አንድ ተማሪ ኮርስ በአንድ ደረጃ በመውሰድ እና በሁለቱም፤ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በኮሚዩኒቲ ኮሌጅ / ዩኒቨርስቲ ደረጃ ክሬዲት ያገኛል።

F. **ከፍተኛ (አድቫንስድ) ምደባ**
አንድ ተማሪ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ በመውሰድ ከቀጣይ አንድ ወጥ የደረጃ መመዘኛ የሚሰጠውን ፈተና በመውሰድ በተቀባዩ የኮሌጅ ትምህርት ተቋም ክሬዲት ሊያሰጥ የሚችል። ኮርሱ በመደበኛ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የተካተቱ በኮሌጅ ቦርድ እና የትምህርት ፈተና አገልግሎት ተቀባይነት ያላቸው ሁሉንም ርእሶችን ኮርሱ የያዘ እና ለአንድ የትምህርት ዓይነት እና በበኮሌጅ ቦርድ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት።

## II. <u>ክፍል የመዝለል የውሳኔ አሰጣጥ ታሳቢ ሁኔታዎች ለአንደኛ እኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች</u>

<u>መዋእለ ሕጻናት- 8 ታሳቢ ሁኔታዎች</u>

1. ወቅታዊ ምርምር ከመዋእለ ሕጻናት- 8 ያሉ ተማሪዎችን የሚከተሉትን ታሳቢ ሁኔታዎች እንዲታዩ ያበረታታል፤ (በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ ተማሪውን ክፍል የማዘለል ውሳኔ ማማከርን፣ ቀደም ሲል የተገኘውን ውጤትን መመልከት፣ የተማሪውን ፍላጎት እና ብስለት የሚያካትት መሆን ይኖርበታል።)

    - የአካዳሚክ ችሎታ፣ አጠቃላይ እውቀት እና ውጤት፤ የተማሪው ውጤት ከክፍል ደረጃው ሁለት ዓመት ይበልጣል ወይ (ችሎታውን በመመዘን እና በክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ መመዘኛ ውጤት)? የሁለት-ዓመት የምክር ሃሳብ ተማሪው በአዲሱ የክፍል ደረጃ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ነው (ይህም የሁለቱን ክፍል ደረጃዎች የፈተና ውጤት በማነፃፀር በአዲሱ የክፍል ደረጃ ከፍተኛ ውጤት በሚያገኙ ተማሪዎች ሊመደብ የሚችል)። የተለያዩ የፈተና ሙከራዎች መጠቀም ይቻላል፤ የግንዛቤ (ኮግኒቲቭ) ችሎታ ፈተና (COGAT) ናጋርሊ ከንግግር-ውጭ አጠቃላይ ችሎታ ፈተና (the Naglieri Non-Verbal Aptitude Test)፣ የዌችስለር የአእምሮ ብስለት ሚዛን ለልጆች (the Wechsler Intelligence Scale for Children) እና ስታንፎርድ -ቢነት (the Stanford-Binet) ። በክፍል ደረጃ እና ከዚያ በላይ ፈተና አሰጣጥ እነዚህን የአይዋ ፈተና ለመሰረታዊ ችሎታ (Iowa Test of Basic Skills)፣ ውድኩክ/ጆንሰን የውጤት ፈተና (the Woodcock/Johnson Test of Achievement) እና ስታንፎርድ የውጤት ፈተና (the Stanford Achievement Test) ሊያካትት ይችላል።

    - የትምህርት ቤት እና የአካዳሚ ታሳቢ ሁኔታዎች፤

        (a) እየታሰበ ያለው የክፍል ምደባ እና የምደባው ማስፈፀሚያ ጊዜ (መከናወን ያለበት ጊዜ በትምህርት ቤት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ መሆን አለበት በተቻለ መጠን የትምህርት አሰጣጡ ከመጀመሩ መጀመሪያ መሆን አለበት።)
        (b) አሁን ያለበት የክፍል ደረጃ የወንድማማች/እህትማማች (ክፍሉን የዘለለው ተማሪ ከእድሜ ከሚበልጠው ወንድም/እህት የማህበራዊና የአካዳሚ ዓለም ውስጥ ሲገባ ሊፈጠር የሚችለውን ነገሮች መመልከት)

ወንድም/እህት ክፍል በመዝለል በአንድ ክፍል ደረጃ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲቀር የምርምር ሪፖርት አጥብቆ ይመክራል።

(c) በትምህርት ቤት መገኘት መከታተል

(d) ፍላጎት፣ ለትምህርት ያለ አመለካከት እና የአካዳሚ የራስ እይታ (ተማሪ ፈቃደኝነት አዲስ ነገሮች ለመጋፈጥ ፣ በመታሰብ ላይ ስላለው የክፍል መዝለል ጉዳይ ያለው ጥሩ አመለካከት)

(e) ከመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ውጭ ተሳትፎ (ልጁ ከትምህርት ቤት ውጭ ያለ የድጋፍ ምንጭ እና ፍላጎት አለው ?) በምርምር እንደታየው በዝቅተኛ ክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የምደባ ውሳኔ የተማሪውን ከመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ውጭ ያለውን ተሳትፎ መመልከት ያስፈልጋል። በክፍል መዝለል ሂደት የእርሱን /የእርሷን ቀጣይ በከፍተኛ ደረጃ የሚያደርገውን ተሳትፎ የሚያስቀር ይሆን?

- የእድገት ታሳቢ ሁኔታዎች፤
  (a) እድሜ - ተማሪው አሁን ባለበት የክፍል ደረጃ ካለው የእድሜ ደረጃ ከአማካኙ በከፍተኛ ውስጥ ነው ያለው?
  (b) የሰውነት መጠን/ የአካል እንቅስቃሴ

- ሁለገብ የመግባባት ችሎታዋች
  (a) የስሜት እድገት/መግባባት ከእኮዮች፣ ከአስተማሪ - ተማሪው የሚያጋጥመው ተፈታታኝ ሁኔታ መቆቆም ይችላል?
  (b) ባህሪ - ተማሪው ምን ያህል ነው ራሱን መግዛት የሚችለው እና በክፍል ውስጥ በሚገባ መስራት የሚችለው?

- አመለካከት እና ድጋፍ
  (a) ከትምህርት ቤቱና ከወላጆች ከሁለቱም ክፍል ለመዝለል ድጋፍ አለ?
  (b) ተማሪው ስለ ክፍል መዝለል/በክፍል ደረጃ ላይ የተመሰረተ ክፍል መዝለል ሃሳብ ያለው ስሜት እንዴት ነው? (በክፍል ደረጃ ላይ የተመሰረተ ክፍል መዝለል በተለምዶ "ክፍል መዝለል" በሚል ይታወቃል። በተለይም የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በመደበኛነት ሊደርስ ከሚችልበት ክፍል በላይ ወደ ከፍተኛ የክፍል ደረጃ መመደብ።)

## III. <u>የአንድ ትምህርት ዓይነት መዝለል</u>

በዚህ አሰራር አንድ ተማሪ ጥንካሬ በአንድ የትምህርት ዓይነት በመሆኑ የእርሱ/የእርሷ ፍላጎት ሊሞላ የሚችለው ክፍል በመዝለል በከፍተኛ ደረጃ ባለው ክፍል የሚሰጠውን የትምህርት ይዘት በማግኘት ነው።

## IV. <u>እድሜው ያልደረሰን በአንደኛ ክፍል መመደብ</u>

የቨርጅኒያ ህግ የሚጠይቀው አንድ ልጅ አምስት ዓመት በሴፕቴምበር 30 ቀን መሙላት አለበት በዚያ የትምህርት ዓመት በመዋእለ ሕጻናት ለመግባት። ይህ ቀን እድሜው ያልደረሰን ልጅ በአንደኛ ክፍል ለመመደብ ይመለከታል። በመሆኑም በሴፕቴምበር 30 ቀን ከአምስት ዓመት በታች እድሜ ያላቸው ልጆች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አይመዘገቡም። አንድ ተማሪ እድሜው ያልደረሰ በአንደኛ ክፍል ምደባ ታሳቢ ሁኔታዎችን የሚያሞላ ከሆነ (እላይ የተጠቀሰውን የእድሜ መስፈርት ጭምር) የዚያ ልጅ ወላጅ/ አሳዳጊ እድሜው ያልደረሰውን ልጃቸው በአንደኛ ክፍል እንዲመደብ በእጩነት እንዲታይ በስፕሪንግ ወቅት ልጁ በመዋእለ ሕጻናት ከመጀመሩ በፊት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ይህም ለምደባ ሂደት እንደሚከተለው ለመፈፀም በቂ ጊዜ ይሰጣል ፤

ወላጆች/ አሳዳጊዎች የሚከተሉትን መፈፀም ይኖርባቸዋል፤

a. የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች የመመዝገቢያ ቅፅ መሙላት፣

b. የልጁን የመዋእለ ሕጻናት ልምድ የሚመለከት የሚከተለውን ሰነድ ማቅረብ፤

- ልጁ የግል ወይም የሕዝብ መዋእለ ሕጻናት ሲከታተል የቆየ ከሆነ፤
    i. ከመዋእለ ህጻናት ትምህርት ቤት አስተማሪ የልጁን የአእምሮ ብስለት፣ አካል፣ የስሜት እና የማህበራዊ እድገት የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ ማምጣት፣
    ii. ልጁ በመዋእለ ህጻናት የሰራቸውን ቢያንስ አራት ስራቸው ማቅረብ የሚኖር ከሆነ። (ናሙናዋቹ በይዘት የተለያዩ መሆን አለባቸው)፣
    iii. የልጁ የእድገት ለውጥ ከትምህርት ቤት ለወላጆች የተላከውን የፅሁፍ ሪፖርት ማቅረብ የሚኖር ከሆነ፣ (ይህም ማንኛውንም ይፋ የግምገማ ሪፖርት ይጨምራል።)
    iv. ልጁን ቃለመጠየቅ ለማድረግ ከርእሰ መምህሩ ጋር ቀጠሮ መያዝ ( እና በርእሰ መምህሩ ከተመደበ ሰራተኛ ጋር ) እና ፤
    v. የምዘና / አጠቃላይ እውቀት(አፕቲቲውድ) / የአእምሮ ብሩህነት አይ.ኪው (IQ) ፈተና ውጤቶች( የሚገኝ ከሆነ)።

- ልጁ የመዋእለ ህጻናት ምንም ያልተከታተል ከሆነ ፤
    i. የልጁን የአእምሮ ብስለት፣ የአካል ፣ ማህበራዊ እና የስሜት እድገት የሚገልፅ በወላጅ ወይም አሳዳጊ አስተያየት የሚገልፅ ጽሑፍ።
    ii. የልጁን ከፍ ያለ እውቀት የሚያሳይ ከመዋእለ ህጻናት ደረጃ የበለጠ የሰራቸውን ቢያንስ አራት ስራቸው ማቅረብ ። (ናሙናዎቹ በይዘት የተለያዩ መሆን አለባቸው)።
    iii. ልጁን ቃለመጠየቅ ለማድረግ ከርእሰ መምህሩ ጋር ቀጠሮ መያዝ ( እና በርእሰ መምህሩ ከተመደበ ሰራተኛ ጋር )፤ እና
    iv. የምዘና / አጠቃላይ እውቀት(አፕቲቲውድ) / የአእምሮ ብሩህነት አይ.ኪው (IQ) ፈተና ውጤቶች( የሚገኝ ከሆነ)

ርእሰ መምህሩ፤

a. እድሜው ያነሰ ልጅ ምደባ ለመመወሰን ይፋ ያልሆነ ምዘና ቴስት ማዘጋጀት፣ ይህ የሚያካትተው የችሎታ ፈተና በትምህርት ቤቱ ሳይኮሎጅስት በግል የሚሰጥ፣ የመዋእለ ህጻናት ማጠናቀቂያ የሂሳብ መመዘኛ ፈተና፣ የፅሁፍ ናሙና፣ ትክክለኛ የፊደል አፃጻፍ እና የንባብ ምዘና በተለምዶ በትምህርት አስተዳደር ዲቪዝኑ የሚሰጥ እና/ወይም የቃላት አወጣጥ መሰረታዊ እውቀት መለያ(PALS) መመዘኛ፤

b. የተሰባሰቡ ሁሉንም መረጃዋች ማጣራት፤

c. ልጁን ቃለመጠየቅ ማድረግ እና አጭር የማስታወሻ መያዝ፣

d. የምደባ ውሳኔ ለመስጠት የተሰባሰቡ ሁሉንም መረጃዋች ከትምህርት ቤት ቡድኑ ጋር ማጣራት ፣ እና

e. ወላጅ(ጆች)/ አሳዳጊዋችን ማግኘት ውሳኔውን በሚመለከት።

## V. የክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) ሂደት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ (ሙሉ ክፍል ወይም አንድ ነጠላ ትምህርት ዓይነት ክፍል መዝለል)

የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) ውሳኔ አሰጣጥ በቡድን የሚከናወን ይሆናል። የውሳኔ ሰጪ ቡድን ርእሰ መምህር፣ የልዩ ችሎታ እና የስጦታ ፕሮግራሙ አስተባባሪ፣ የተማሪው ወላጅ/ አሳዳጊ እና የተማሪውን የትምህርት ቡድን ይይዛል። ይህም የሚያካትተው የተማሪውን የወቅቱ አስተማሪ፣ የልዩ ችሎታ እና የስጦታ ፕሮግራሙ ተወካይ፣ የት/ቤት ሳይኮሎጅስት፣ የትምህርት ቤት አማካሪ፣ የልዩ ትምህርት እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ(EL) ባለሞያ (አስፈላጊ ከሆነ) እና የሚዛወርበት ክፍል አስተማሪ(ዎች) ነው።

1. የክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ሂደት የሚጀምረው የክፍል መዝለል የፅሁፍ ጥያቄ ከወላጅ/አሳዳጊ ወይም ከአስተማሪ(ዎች) ለርእሰ መምህሩ ሲቀርብ ነው ።

2. ርእሰ መምህሩ ለቀረበው ሃሳብ የችሎታ እና የውጤት መመዘኛ ቴስት፣ ከወቅቱ አስተማሪ እና ሌሎች ስለተማሪው ትምህርት እና አካዳሚ ትውውቅ ካላቸው የእድገት ለውጦች እና የአካዳሚ የእድገት ታሳቢ ሁኔታዎች፣ የመግባባት ችሎታዎች፣ የተማሪው አመለካከት እና የተማሪው አስተሳሰብ መረጃ ማሰባሰብ እና የአይዎ ክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ሚዛን (*Iowa Acceleration Scale*) እንደ መሳሪያ በመጠቀም በትምህርት ቤት ደረጃ ድጋፍ ስለመኖሩ መረጃ በማሰባሰብ ጥያቄው በቀረበ በ45 ቀናት ውሳኔውን መስጠት ማከናወን።

3. ተማሪው ክፍል ለመዝለል(አክስለሬሽን) ጥሩ እጪ ከሆነ (በአይዋ ክፍል መዝለል (አክስለሬሽን) ሚዛን በተገኘው አጠቃላይ ውጤት እና በትምህርት ቤቱ እና የወላጅ-መሰረት የውሳኔ ሃሳብ ቡድን በተወሰነው መሰረት) ከዚያ የክፍል መዝለል የፅሁፍ እቅድ(WAP) መዘጋጀት ይኖርበታል እና የልጁን የትምህርት ሂደት ለመከታተል አገልግሎት ላይ ይውላል። ይህም ሙሉ ክፍል የትምህርት ይዘት አለመዘለሉን ነገር ግን የሚሰጠውን የትምህርት እውቀት መጠን የመጨመር ስራ ያረጋግጣል። በተለይም አግባብነት ያለው የቅድመ ምዘና/መለያ(Diagnostic) ምዘና ሂደት በእቅዱ ውስጥ ማካተት፣ በክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) ምክንያት አንድ ችሎታ እውቀት ሊዘነጋ የሚችል ወይም ያልተካተተውን በትክክል ማስተማር ወይም በድጋሚ ማስተማር ተማሪው በትክክል የተረዳው መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ እቅድ በትምህርት ቤት ደረጃ አስተዳደር፣ የክፍል ደረጃ አስተማሪ እና ልዩ ስጦታ ያላቸው ተማሪዎች አስተማሪ መዘጋጀት ይኖርበታል። በዚህ እቅድ ላይ ክትትል መደረግ ይኖርበታል እና በየዓመቱ መሻሻል ይኖርበታል ትክክለኛ የአካዳሚ መንገድ ለመከተል ለተማሪዎች የወደፊት ሁኔታ የWAP የተፈረመ አንድ ኮፒ በተማሪው ቆሚ ሪከርድ መዝገብ መቀመጥ ይኖርበታል።

4. ክትትል የሚደረግበት የመሸጋገሪያ ጊዜ ለ30 ቀናት ያልበለጠ መካሄድ ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ ወላጆች አስፈላጊ ከሆነ የክፍል መዝለሉን የማስቀረት ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

5. ይህ ሂደት በፍትሃዊነት እና ስርዓት ባለው መልክ ለሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት ይሰራል።

## VI. በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የክፍል መዝለል(አክስለሬሽን)

የክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) ውሳኔዎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አሁኑ ካሉበት ክፍል በቀጣዩ ከፍተኛ ክፍል እንዲከታተሉ የመመደብ ስራ በቡድን የሚከናወን ይሆናል። የውሳኔ አሰጣጥ ቡድን የሚያካትተው የልዩ ችሎታ እና የስጦታ ፕሮግራሙ አስተባባሪ፣ የተማሪው ወላጅ/ አሳዳጊ፤ እና የተማሪው የትምህርት ቡድን ነው። ይህም የሚያካትተው የተማሪው የወቅቱ አስተማሪ፣ የልዩ ችሎታ እና የስጦታ ፕሮግራሙ ተወካይ፣ የት/ቤት ሳይኮሎጅስት፣ የትምህርት ቤት አማካሪ፣ የልዩ ትምህርት እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) ባለሞያ (አስፈላጊ ከሆነ ) እና የሚዛወርበት ክፍል አስተማሪ(ዎች) ነው።

ታሳቢ ሁኔታዎች የተማሪው ብስለት የሚመለከቱ እና በትምህርት ዓይነቱ ቀደም ሲል የተገኙ ውጤቶችን ከክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) ጥያቄ ጋር መታየት ይኖርባቸዋል። ብስለትን የሚገልፁ መመዘኛዎች ሊያካትቱ የሚችሉት የአስተማሪ የድጋፍ ደብዳቤ፣ የአስተማሪ እና/ወይም የአማካሪ እይታ (ፕሮፋይል) እና ተዛማጅ መረጃዎች የተማሪውን ችሎታ በክፍል መዝለል ተጠቃሚ ስለመሆኑ የክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) በተመለከተ (ለምሳሌ፤ ከመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎችን፣ የአማካሪ ገፅታ እና የመሪነት ሚናዎች) ናቸው።

የጥምር ምዘገባ ኮርሶች ተማሪዎችን የሚጠይቀው ወደ የኮሚዩኒቲ ኮሌጅ NOVA ማመልከትን እና በቨርጂኒያ ምድባ ፈተና (Virginia Placement test) አግባብነት ባለው ደረጃ መመደብን ይጠይቃል። ተጨማሪ ቅድመ-ታሳቢ ሁኔታዎች የከፍተኛ ደረጃ ኤ.ፒ. (AP) ወይም የጥምር ምዘገባ ኮርሶች የሚመለከት ከሆኑ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት ዓይነት ፕሮግራም ውስጥ ይገኛል።

## VII. የይግባኝ አሰራር ሂደት

የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ በወላጅ/ አሳዳጊ ይግባኝ እንደአስፈላጊነቱ ለአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር በፅሁፍ ሊቀርብ ይችላል። የክፍል መዝለል ሂደቱን ማንኛውንም የአሰራር ክፍል እንደገና እንዲታይ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል የሚከተለው ዓይነት፤

1) የመረጃ አሰባሰብ ሂደት፣
2) የኮሚቴ ስብሰባ ውጤት ሂደት እና፣
3) የክፍል መዝለል(አክስለሬሽን) በፅሁፍ የተዘጋጀው እቅድ

ወላጅ/ አሳዳጊ የሚያሳስባቸውን ጉዳዮች የሚዘረዝረውን ማመልከቻ ለርእሰ መምህሩ ካስገቡ በኋላ ከወላጅ / አሳዳጊ ጋር ስብሰባ ይደረጋል ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ሊጨምር ይችላል በጉዳዮ ላይ ለመወያየት።

የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር እንደአስፈላጊነቱ ይግባኙ በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ የመጨረሻውን ውሳኔ በፅሁፍ ይሰጣል። ይህ የፅሁፍ ማስታወቂያ የውሳኔውን ምክንያት ማካተት ይኖርበታል።

| | |
|---|---|
| የፀደቀው፤ | ጁን 22፣ 2017 |
| የሕግ ማጣቅሻ፤ | የቨርጅኒያ ህግ 1950፣ እንደተሻሻለው § 22.1-78<br>(8) -131-50<br>(8) -131-90<br>(22) -180-10 |

| | | |
|---|---|---|
| የቃላት መፍቻ፤ | IGBB | ልዩ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች |
| | IKE | የአካዳሚ ለውጥ እና መድገም |
| | IKE-R | አካዳሚ ለውጥ እና መድገም ደንቦች |
| | IKEB | ክፍል መዝለል |
| | JO | የተማሪዎች ሪኮርድ |

የአካዳሚ ማጣቀሻ፤ አይዋ አክስለሬሽን ሚዛን (Iowa Acceleration Scale)፣ 3ኛ እትም ቅፅ : የሙሉ ክፍል መዝለል አክስለሬሽን መመሪያ (A guide for Whole-Grade Acceleration K-8. 2009). The Connie Belin & Jacqueline N. Blank International Center for Gifted Education and Talent Development.

አይዋ አክስለሬሽን ሚዛን (IAS) እንደ አቅጣጫ አመልካች መሳሪያ በመጠቀም የሚከተሉት ቀጣይ ሂደቶች መከተል ይኖርበታል ከክፍል ደረጃ ውጭ ምደባ ውሳኔዎች በሚሰጥበት ወቅት፤

